የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

# በሊቢያ እስር ቤቶች ያሉ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ደህንነት አሳሳቢ አደጋ ላይ ወድቋል

የካቲት 17 ቀን 2003 ዓ. ም.

በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን እና ኤርትራዊያን ስደተኞች በሊቢያ በረሃ ውስጥ በኮንቴኔሮችና በሌሎችም እስር ቤቶች ተይዘው ይገኛሉ። ሊቢያ ቀውስ ውስጥ መሆኗና የኢትዮጵያ ፓስፖርት የያዙ ቅጥር ነፍስ ገዳዮች ቤንጋዚ ውስጥ ተይዘዋል መባሉ፣ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ለጅምላ ጥቃት ዒላማ ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው ስጋታችንን ያብሰዋል። ኢፖእአኮ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን የስደተኖቹ ደህንነት መጠበቁን እንዲያረጋግጥና ዜጎቻቸውን ከሊቢያ እያወጡ ያሉት ሀገራትም ለስደተኞቹ ይህንኑ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል።

ከዚህ በፊት የሊቢያን አገዛዝ ዘረኝትና የ"ጥቁር አፍሪካዊያንን" ጉዳይ በንቀት ሲያስተናግድ ታዝበናል። በሊቢያ ማህበረሰብም ውስጥ ይህንኑ አግባብ ያልሆነ አመለካከት የሚጋሩ ሰዎች አሉ። ሰሞኑንም የጋዳፊ አገዛዝ ተቃዋሚዎችን ለመግደል የኢትዮጵያ ፓስፖርት ይዘው የተገኙ ሰዎችን ጨምሮ "አፍሪካዊያን ቅጥር ነፍሰ-ገዳዮችን" አሰማርቷል መባሉ በትሪፖሊ፣ ኤል ቢዳ እና ሌሎች ቦታዎችም ያሉ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ላይ የብቀላ ጥቃት ሊዘነዘርባቸው ይችላል የሚለውን ስጋት ከፍ ያደርገዋል።

ኢፖእአኮ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን እና ምዕራባበዊያኑ ሀገሮች በሊቢያ እስር ቤቶችና ከተሞች ያሉ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን ደህንነት እንዲያረጋግጡ ጥሪውን ያቀርባል።

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM